NSW Education Program on FGM

NSW GOVERNMENT Health Western Sydney Local Health District

# ማስታወቂያ

## ዛሬም ይሁን ለወደፊቱ ሴቶች ልጆቻችሁን ጠብቁ!!!

የሴቶች ግርዛት የልጃገረዶች ወይም የሴቶችን ሰብዓዊ መብቶች መተላለፍ ነው።

የሴቶች ግርዛት በዓለም ዙሪያ በሚፈጸምባቸው ሀገሮች ብዙ የሞትና የረጅም ጊዜ የጤንነት ጉዳት በልጃገረዶች ወይ በሴቶች ላይ የሚያስከትል ጎጂ ባሕላዊ ተግባር ነው።

በአውስትራሊያ ውስጥ የሴቶች ግርዛት ተግባር ሕገ ወጥ ነው። ልጃ ገረዶችን ወይም ሴቶችን መገረዝ ሕጋዊ አይደለም።

ልጃ ገረዶችን ወይም ሴቶችን ከአውስትራሊያ ውጭ ወስዶ በሌላ ሀገር ውስጥ ማስገረዝ በሕግ የተከለከለ ነው፣ ያስቀጣል።

በአውስትራሊያ ውስጥም ሆነ ወይም ከአስትራሊያ ውጭ ሴቶች ልጆችን ወስዶ ማስገረዝ ቅጣቱ የ 21 ዓመታት ዕሥራት ነው። ይህ ቅጣት የግርዛት ተግባር በፈጸሙት ላይና ተባባሪዎች በሆኑት ላይም ይጸናል።

ብዙ የዓለም ሀገሮች ይህን የሴቶችን ግርዛት የሚከላከል ሕግ አላቸው። ስለዚህ ሴቶች ልጆቻችሁን ለማስገረዝ አትወስኑ፣ ተግባሩንም አትፈጽሙ።

ሴት ልጆቻችሁን ይዛችሁ ለዕረፍት ወደ ውጭ ሀገር ቢትሄዱም እዚያ ሳላችሁ እንዳታስገርዙ።

ምናልባት የገርዛቱን ተግባር ሊፈጽሙ በሚችሉ ዘመዶች ዘንድም ሴት ልጆቻችሁን አትተው። ብዙ ጊዜ አያቶችንና አክስቶችን መጠንቀቅ ነው።

## ሴቶች ልጆቻችሁን ከዕድሜ ልክ ሥቃይና እርስዎን ራስዎትን ከ21 ዓመታት ዕሥራት ይጠብቁ፣ ያድኑ!!!

ለበለጠ መረጃና ለዕርዳታ ፍለጋ በNSW የሴቶች ግርዛት (FGM) መከላከያ ትህርታዊ መግለጫ ፕሮግራም በስልክ ቁጥር፥ **02 9840 3910** ይደውሉ ወይም የተተረጎመውን የሴቶች ልጆችን ግርዛት አስመልክቶ የወጣውን ሕግ በዌብ ሣይታችን (web site) ይመልከቱ።

**በኒው ሣውዝ ዌልስ የሴቶች ልጆች ግርዛት መግለጫ ፕሮግራም**
**The NSW Education Program on FGM.**